# በዘር መከፋፈል አምባገነን ሥርዓትን ያጠናክራል

ግንቦት 2002 ዓም

ለዓይን የሚያስጠይፍ፤ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ፤ አፍንጫ የሚሰነፍጥ፤ አገር የሚያስጠፋ፤ ትውልድ የሚያስመትር ከድንቁርናና ከራስ ወዳድነት ብሎም ከባዕድ ቅጥረኝነት ከሚወለዱ በሽታዎች ሁሉ እንደ ዘረኝነት የከፋ የለም።

ባለፉት አሥራ ዘጠኝ የወያኔ መርገምት ዓመታት ታሽተንበታልና፤ ተንገላተንበታልና፤ ትኩሱ ጉልበታችን ተዳክሞበታልና፤ ለዚህም ነው ወግድ ጎጠኝነት ብለን ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያን አስቀድመን ኢወክንድ የሆንነው። በኢሕአፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት ጥላ የተሰባሰብን የትውልድ አደራ ተረካቢዎች የነፃነትን ትርጉም ዕድሜ ለቀደምቶቻችን ተረድተነዋልና፤ በአንድነት፣ በኢትዮጵያዊነት ተደራጅቶ መታገልን የመሰለ ባርነትን መላቀቂያ አቋራጭ ጎዳና ከቶውንም የለምና፤ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በክልል መከፋፈል - በወጣቱ ቋንቋ - ጤባ አመጣሽ ዘይቤ ብለነዋል።

ኢትዮጵያን ከካርታ ሕዝብዋን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ከዘመናት ጠላቶቿ ቀብድ በልቶ የሚንደፋደፈው የወያኔ ሥርዓት እኛ ወጣቶቹን እንዳናብር በዘር፤ ለሃገር እንዳናስብ በክልል፤ እንዳንግባባ በቋንቋ ከፋፍሎና ሸንሽኖ አሥራ ዘጠኝ ቀን መቀመጥ የማይገባው ገለባ ሥርዓት አሥራ ዘጠኝ ዓመት በላያችን ላይ ተቆጠረብን። በዕውነት አፍረናል።

መሬቱን ገለባ ያርግላቸውና ስመ ጥሩዎቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች የአፍሪካ የትግል ቀንዲል የነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የከፈሉት ክቡርና ንዑዱ መስዋዕት በኢትዮጵያዊነት እንጂ ከቶውንም በዘረኛነት አልነበረም - ከተማሪው መሪ ጥላሁን ግዛው እስከ ወጣቱ ባቢሌ ኃ/ሥላሴ፤ ከሠራተኛዋ ዳሮ ነጋሽ እስከ ተማሪዋ መነን ኃይሉ፤ ከሙደስር ዑስማን እስከ እጅጋየው ደበላ፤ ከነገመቹ እስከ አሕፈሮም ሃብተ ሥላሤ፤...ወዘተረፈ።

ከኤርትራ ትግራይ፤ ከጎንደር ጎጃም፤ ከሲዳሞ ባሌ፤ ከሐረር ጋምቤላ፤ ከስድስት ኪሎ አራት ኪሎ፤ ከልዑል መኮንን እስከ ተፈሪ መኮንን፤ ከደሴው ወይዘሮ ስህን እስከ አዳማው አፄ ገላውዲዎስ፤ ከጅማው ሚያዘያ ሃያ ሰባት እስከ ሐረሩ መድኃኔ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ...ተማሪዎች የትግላቸው

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040
e-mail: join@eprpy.com www.eprpy.com

መነሻና መድረሻ ኢትዮጵያ ነበረች። ዲሞክራሲም ነበር መፈክራቸው ። ታዲያ እነዚህ ትንታግ ቀደምቶቻችን በቅለው በረገፉባት ምድር፤ ባፈሰሱት ደማቸው ላይ ቆመን የዘንድሮ የስድስት ኪሎ ተማሪዎች የወያኔ ዘረኛ ፓሊሲ ሰለባ ሆነን በዘር ተከፋፍለን መጋደል ነበረብን? ይህ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በሙሉ የቀረበ የስብዕና ጥይቄ ነው ። እኛ ኢወክንዶች ወያኔ አፍራሽ የዘረኝነት በሽታ ተላላፊ ሆኖ እርስ በርስ ለተፋጁና ሰለባ ለሆኑት ሃዘናችንን ብንገልጽም ከሃዘኑ በላይ መሪር ሃዘን የሆነብን የቀደምቶቻችን የኢትዮጵያ ተማሪዎች የአንድነት ትግል ታሪክ ላይ ቆሻሻ ጠባሳ መጣሉ ነው።

በዘር መከፋፈል ብሎም ደም መፋሰስ ጠቀሜታው ነፃነቱን በወያኔዎች ለተገፈፈው ሕዝባችን ሳይሆን ለራሱ ለገፋፊው ሥርዓት ነውና ይህ ትግል ሳይሆን ከንቱ ልፊያና በከንቱ የፈሰስ የጅል ደም ብለነዋል። ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም የተደራጀ ሰይጣን ሥርዓት እንጂ ለትግራይ ሕዝብ የመጣ እንዳልሆነ ሁሉ ለኦሮሞውም ለአማራውም ለሌላውም የማይበጅ መሆኑን እንደኛ ተረድታችሁ፤ እራሳችሁን በኢወክንድ ሆነ በሌላም አደራጅታችሁ፤ በዚህም ለኢትዮጵያ ወጣቶች በሙሉ በልዩነታችን ላይ ሳይሆን በአንድነታችን ላይ የተማከለ ትግል እንጂ ወያኔ በጋተን የዘረኝነት መርዝ መሳከርና መጫረስ ትርፍ የለውምና ይህንን የአሥራ ዘጠኝ ዓመት የጨለማ ጉዞ በአንድነት አብረን ለኢትዮጵያ ብርሃን እንድናደርግ ነው የመጨረሻ ጥሪያችን።

ኢትዮጵያዊ ከሆናችሁ፤ ዘረኝነት ከኮነናችሁ፤ የወያኔ ሥርዓት የሕዝብና የታሪክ ጠላት መሆኑን ተረድታችሁ ይህንን ሥርዓት ለማስውገድ ከቆረጣችሁ፤ በያላችሁበት ኢወክንድ ናችሁና የመንፈስ ቁርኝታችንን አጠንክረን በስልትና ወጣታዊ ቅልጥፍና አካላዊ ትስስራችንን አጥብቀን በኢትዮጵያዊነት ኩራት ዘረኝነት የሰበረውን መንፈሳችንን እንደምናጠናክርና በጋራ ለጋራ ሃገራችን የትንሳዔን መዝሙር የምንዘምርበት ቀን ሩቅ አይሆንም እንላለን።

ዘረኝነት ይሠበራል፤
ኢትዮጵያዊነት ያብባል

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት*

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040
e-mail: join@eprpy.com www.eprpy.com